# ሕብረት እንዴትና ከማን ጋር?

አገራችን ኢትዮጵያ የገጠሟትን ውስብስብ ችግሮች ለማስወገድ አብሮ መስራት ወሳኝ መሆኑን የተረዱና፤ተረድተውም በሃሳቡ ተመርተው በአንድ ላይ በመደራጀት ፣በፖለቲካው ትግል ውስጥ ገብተው አለአንዳች ውጤት  እንደጉም በነው የጠፉ ብዙዎች ናቸው።በተደጋጋሚ የሕብረት ጥሪ ይሰማል፤የዚያን ያህል በድርጅቶችና በአባሎቻቸው ላይም የህብረቱን ጥሪ ለማስተናገድ ጫናው ተበራክቷል።ትግሉ ትክክለኛውን ፈለግ ይዞ ይሂድ ሲባል ትክክለኛው ሕብረት እንዴትና በምን ሁኔታ እንደሚፈጠር ተፈጥሮም ዕድሜ እንዲኖረውና ከግቡ እንዲደርስ ብልሃትና ስልት ያስፈልጋል።ይህን ሳያረጋግጡ ለዜና ፍጆታ ብቻ መሰረት የሌለው ስምምነት ላይ ቢደረስና ሕብረት ተፈጠረ ቢባል ሕብረቱ ወደለመድነው ውድቀትና ተስፍ አስቆራጭ ውጤት ያሽጋግረናል።

በአገራችን ስለሕብረት ስናነሳ በ1997 ዓ.ም.(2005 እ.አ.አ.)ቅንጅት በሚል የተጣመረው ስብስብ በሕዝብ ስነልቦና ውስጥ ሊያድር የቻለው የታመቀው ብሶት የፈጠረው ታሪካዊ አጋጣሚ ስለነበር ነው።ይህ ስብስብ በመከራ ሲፈተን በዓላማ ጽናትና በአመራር ውስጡ ሲፈተሽ ባዶ ሆኖ ተገኘ።በቀውጢ ወቅት ለሕዝብ አለኝታ መሆንን፣አደራ መቀበልን፣ለሃላፊነት ብቁነትን ማሳየት ቀርቶ ወደ ክህደት ተለወጠ።ዛሬም የዚያኑ ወቅት ችግር ተከትሎን ይዞራል።ከእጃችን የወጣውን መልሰን በመፈለግ ላይ በመሆናችን ማንኛውንም ሕብረት፣ስብስብ፣ውህደት እንመኛለን።ይህ ትውልድ ከስህተቱ ተምሮ ብልሃት ካላፈላለገ ሲዋልልና የሚመኘውን ሳያገኝ መኖሩ ነው።ለአንዲት ኢትዮጵያ፣ለአንድ ሕዝብ፣ለአንድ አገር በሚለው መንፈስ ተመርቶ እምነት ሊጣልበት የሚችል ስብስብ የመፍጠሩ ሃላፊነት ብሔራዊ አጀንዳችን በመሆኑ ሕብረቱ እውን እስኪሆን ድረስ ትግላችን መቀጠል ይኖርበታል።

በአገሪቱ ኤኮኖሚያዊና የማህበራዊ ኑሮ ፍትሕ እንዲኖር፣አገሪቱ ባላት አቅም ዜጎቿን ያለአንዳች አድልኦ የምትንከባከብ፣በየትኛውም የኢትዮጵያ ምድር ሰርተው ለማደር ያላቸውን መብት የምታውቅ፣በፖለቲካ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ተቋሞች ውስጥ የመካፈል፣የመምራት፣የመምረጥና የመመረጥ መብት እንዲረጋገጥ፣በብሔር በጾታና ሃይማኖት የተነሳ ልዩነት የማይደረግባት አገር እንድትሆን የማድረጉን ሃላፊነት ሊያረጋግጡ የሚችሉ ፓርቲዎች በሌሉበት ቦታ ደካሞችና ብሔራዊ እራዕይ የሌላቸው ሕዝቡ ለሕብረት ያለውን ጉጉትና ፍላጎት በመጠቀም ውዥንብር በመፍጠር ለዳግመኛ ተስፋ አስቆራጭ ተግባር   ይሰለፋሉ።

ከግለሰብ ነጻነት ይልቅ የድርጅት ነጻነት ለማስከበር በዘር ሃረግ ተደራጅቶ ዲሞክራሲ መገንባት ይቻላል የሚለው የወያኔ ብገርት በሕገመንግስቱ ከተደነገገ ወዲህ የኢትዮጵያዊነትን ትግል ከፍተኛ ችግር ውስጥ እንዲገባ ተደርጓል።አገዛዙ ዜጎች በዘራቸው ተደራጅተው በተሰመረላቸው ክልል ውስጥ ታግደው የፖለቲካ ተሳትፎ ማድረግ ይችላሉ የሚለው የከፋፍለህ ግዛ ጽንሰሃሳብ(ዶክትሪን)ኢትዮጵያን እንደ አገር የማቆየት ተስፋ እያጨለመው ነው።በዚህ በወያኔ ዶክትሪን የተደራጁ የኢትዮጵያዊነት መፍትሄ ጎልቶ እንዳይወጣና እንዳይደመጥ አድርገውታል።

በአገራችን ላለፉት 23 ዓመታት የተፈጠሩት ድርጅቶች በአብዛኛው ከወያኔ አስተሳሰብ ጋር አመለካከታቸውን አስተካክለው የሚራመዱ ናቸው።በቅንጅት እራዕይ ተካተው የነበሩት እንኳን ሳይቀሩ በኢትዮጵያዊነት መተማመን ተስኗቸው ተመልሰው የተደበቁት በጎሳ ድርጅት ስብስብ ውስጥ ነው።ሃቅ ይነገር ከተባለ መኢአድ ብቻ ነው ከነበረውና ካለው የኢትዮጵያዊነት መንፈስ ያላፈገፈገው።ባለፉት 5 ዓመቶች በመኢአድ ዙሪያ ብዙ ከበባዎች ተካሂደዋል።እስከዛሬ ድረስ ኢትዮጵያዊነት ከጎሳ ድርጅቶች ጋር ይደራደርና ወያኔን በራሱ ሜዳ ይግጠም የሚለውን ስንኩል አስተሳሰብ የሚገፋው ወገን በታሪክ ይቅር የማይባል በደል ሲፈጽም ቆይቷል።ለዚህ በአስረጅነት የአንድነትና ፍትህ ፓርቲና ( UDJ )የትግል አጋሮቹ የያዙትን የፖለቲካ መስመር ቀረብ ብሎ መመልከቱ በቂ መረጃ ነው።

በእኔ እይታ የመኢአድና የአንድነትና የፍትህ ፓርተ የውህደት ድርድር በተያዘው መንገድ ከቀጠለ ፍሬያማ አይሆንም ብዬ እሰጋለሁ፤የማይሳካበትንም ምክንያቶች በሚከተሉት ነጥቦች አስረዳለሁ።

1. መኢአድና የአንድነትና የፍትህ ፓርቲ ቀደም ባሉት ጊዜያቶች ሁሉ በኢትዮጵያ የፖለቲካ አድማስ ውስጥ የጋራ አቋም ይዘው አያውቁም።በአገሪቱ ወሳኝና ብሔራዊ አጀንዳዎች ዙርያ

የጋርዮሽ አመለካከት አፍልቀው ሕዝብን ቀስቅሰው ፣አስተምረው አያውቁም።በቅርቡ በባሕርዳር የተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ በልዩነቶታቸው ዙሪያ ሲሰሩ የነበሩ ድርጅቶች አሁን ተቀራርበው በሕዝብ ፊት ታማኝነት ያለው ተግባር ለማከናወን ቆርጠው ተነስተዋል ከሚለው መደምደሚያ ላይ ሊያደርስ አይችልም።በቅድሚያ አገሪቱ የገባችበትን ቀውጢ ሁኔታዎች በመግለጽ ከዚያ ለመውጣት የተለሙትን የጋራ ዕራእይ ይፋ አድርገው በኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት በተግባር መፈተሽ ይኖርበታል።

2. የውህደቱ ድርድር አንተም ተው አንተም ተው በሚል ሽምግልና የተከናወነ ለመሆኑ ሁለቱም ፓርቲዎች ገልጸዋል።ለምርጫ ተሳትፎ ለማመቻቸት ብቻ ታስቦ የሚደረገው ውህደት በቅድሚያ ኢትዮጵያዊነትን መርህ ካላደረገ መሰረቱ ያልጠና ሂደት ይሆናል።የውህደቱ መሰረት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን መሰረት ያደረገ መሆን ይገባዋል።የጠላቴ ጠላት የሚለው አስተሳሰብ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል።ምርጫውና የሁለቱ ድርጅቶች ውህደት አብሮ መያያዝ የለበትም፡፤ከምርጫውም በኂላ በቀጣይነት መኖር የሚገባው እንጂ ጨዋታ ፈረሰ ዳቦ ተቆረሰ እንደሚባለው የልጆች ጨዋታ በምርጫው ማግስት የሚበታተን አጭር ዓላማ ያነገበ መሆን አይኖርበታም።ውህደቱ የወያኔን መንግስት በሌላ መንግስት ለመተካት ብቻ ሳይሆን በወያኔ ስርዓት ኢትዮጵያ ያጣችውን ክብርና ነጻነት አስመልሶ ለወደፊትም እንዳይደፈር የሚንከባከብ ስርዓትና መንግስት እንዲኖር ማድረግ ነው።ከምርጫው በፊት አገራዊ አጀንዳ መቅደም ይኖርበታል።ስለምርጫ መቅረብ መራቅ እያወሩ ውህደት ማካሄድ ድርድሩን የወያኔ ወዳጆች የያዙት ያስመስለዋል።መድረክ አላንዳች ቅድመሁኔታ በመጭው ዓመት በወያኔ የምርጫ ድግስ ለመሳተፍ ወስኗል፤የዚሁ አካል የሆነው አንድነትና ፍትህ ፓርቲ(ዩዲጄ)ምርጫው ዕድላችን ነው በሚል መኢአድን ለመሳብ መቻሉ ውህደቱ በቀጥታ የመድረክ ተቀጽላ እንደሚሆን ግልጽ ምልክቶች ይታያሉ።ሽምግልናውና ተደራዳሪዎቹ ሃቀኝነት ይጎድላቸዋል።

3. መኢአድና የአንድነትና የፍትህ ፓርቲ በጋራ ደርሰንበታል የሚሉት ስምምነት ግልጽነት የለውም።ለአባሎቻቸውና ለደጋፊዎቻቸው የደበቁት ጉዳይ አለ።ቀደም ባሉት ጊዜያቶች መኢአድ ለድርድሩ ያቀረበውን ሁኔታ ኡዴጀ መልስ አልሰጠበትም።ኢዴጀ መድረክ ጋር ያለውን ስሙንና ሕጋዊ አባልነቱን ለመሰረዝ የሚያበቃ በቂ ስራ አልሰራም፤ያንንም ለማድረግ ፍላጎቱን በይፋ አልገለጸም።ከመድረክ ወጥቻለሁም ብሎ ያቀረበው ማስረጃና የሰጠው መግለጫ የለም።አንድ ድርጅት ካለበት ስብስብ ሳይወጣ ከሌላ በዓላማ ከማይጣጣም ስብስብ ውስጥ አይቀላቀልም።የመድረክና የመኢአድ ራዕይ የተለያዩ መሆናቸው ሲታወቅ ኡዴጄ ሁለቱንም ለማገልገል ወይም ለማስተናገድ ያሰበ ይመስላል።በሁለት ባላ ላይ መቆም አይቻልምና አንዱን መምረጥ አለበት።

4. ሁለቱም ፓርቲዎች አባልና መዋቅር፣የውሳኔ ሰጭ አካል አለን ካሉ ከፈረሱ በፊት ጋሪውን አደረገ ውሳኔ ላይ መድረስ አልነበረባቸውም።በፊርማ ጸድቆ፣በመገናኛ ተቋማት አዋጅ!አዋጅ! የተባለለት ውሳኔ የፓርቲዎቹን የላዕላይ ምክር ቤት የስራ ድርሻና ሃላፊነት የጣሰ ነው።በመሆኑም ፓርቲ አፍርሶ ፓርቲ ለመገንባት አመራሩ በሽምግልና የሚፈጽመው ሳይሆን በፓርቲዎች ዴሞክራሲያዊ የውሳኔ አሰጣጥ መስተናገድ ይገባው ነበር።ይህ ባለመሆኑ ቀጣዩን እርምጃ እያከበደው መጥቷል።

5. የትግሬ ወያኔ አገዛዝ ስለፓርቲዎች ምስረታ የደነገገው ጸረዲሞክራሲያዊ ሕግ በፓርቲዎች ውህደት ላይ እቀባ አለው።ከላይ እንደተገለጸው ዩዲጄ በሁለት ድርጅቶች ውስጥ ሊገባ አይችልም።ፓርቲዎችን አፍርሰው አዲስ ስም ይዘው ከወጡ በቁጥር አራት የተገለጸው ውሳኔ መኖር ይገባዋል።ይህ ማለት ተከታይ መዘዝ አለው።ሁለቱም ፓርቲዎች ስማቸውን አስረክበው ለመራመድ በላዕላይ ምክር ቤቱ ማጽደቅ ይኖርባቸዋል።ይህን አድርገው ቢቀጥሉም ወያኔ ባለው ባህሪና በየፓርቲዎች የሚቀሩት አማጽያንና አድርባዮች ተሰበጣጥረው የፓርቲዎቹን ስም ይዘው እንዲንቀሳቀሱ ማድረጉ አይቀርም፤ይህ በቅንጅትም፣በሌሎቹም ድርጅቶች የታዬ የተለጣፊ ፈጠራ ሂደት ነው።ይህ ከሆነ የደረሱበት ስምምነት ለቀጣይ የተጠናከረ ትግል ሳይሆን ከወያኔ ጋር ለሙግት ይዳርጋቸዋል ማለት ነው።

የመኢአድንና የአንድነትና ፍትህ ፓርቲ ውህደትን በግንባር ቀደም ከደገፉት አንዱ ሸንጎው ነው።ሸንጎው በተቀዳሚ ለተቃዋሚ ድርጅቶች የአንድነትና የህበረት ክንውን ተሟጋችና ደጋፊ በመሆኑ በሁለቱ ፓርቲዎች መካከል የተጀመረውን ውይይትና ጋዜጣዊ መግለጫ ተንተርሶ

የሰጠው ድጋፍ ቀናነት የተመላበት ነው።በኢትዮጵያ የፖለቲካ ስልጣን ሽግግር ሊደረግ ይችላል ብለን የምናይበት አመለካከታችን ከወያኔ ተጽእኖ ነጻ የሆነና የኢትዮጵያዊነት መንፈስ የተላበሰ አማራጭ ተፈጠረ ሲባል ድጋፍ መስጠት ተገቢ ነው።የኢትዮጵያዊነት አደራ ይዘው በሃቀኝነትና በግልጽነት የሕዝብ አመኔታ አትርፈው ለመጓዝ ለሚነሳሱ አይዟችሁ ሊባሉ ይገባል።

የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዊነት ድርጅታዊ ቅርጽ ይዞ፣በዓላማ ጸንቶ ዴሞክራሲያዊ ተመክሮዎችን መመሪያ ያደረገ ስብስብ ተመስርቶ ማየት እንደማይፈልግ ሁላችንም እናውቀዋለን።በመሆኑም ወያኔ ወደአዘጋጀልን ወጥመድ ውስጥ እራሳችንን እንዳናስገባ ጥንቃቄ ማድረጉ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ከመሆኑም በላይ ለሚደረገው የትግል ስኬት ዋስትና ነው።

በአገራችን ኢትዮጵያ የዜጎቿ መተባበር እውን ይሁን ስንል ውስብስብ ችግሮችን የመፍታት ችሎታችንን አበልጽገን፣የሚገጥሙ ችግሮችንም በቅድሚያ ገምተን ለመከላከል ዝግጁ ሆነን መገኘት ይኖርብናል።ይህን ሳናደርግ በየዋህነትና በቅንነት ብቻ መልካም ገጹን በማሰብ ከተዘረጋ ወጥመድ ውስጥ መግባት ስለሚከተል መጠንቀቅ ይጠቅማል።በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ የሚፈጠሩ ህብረቶችን አጨብጭቦ ከመቀበል በፊት ከያቅጣጫው መፈተሽ ይኖርባቸዋል። ከስህተታችን እየተማርን፣ እየወደቅን እንነሳለን የሚለውን ዝንባሌ በመቀበል ለበለጠ ውድቀት በር መክፈት አይኖርብንም።ተሳስቶ ከመታረም ይልቅ ላለመሳሳት ጥንቃቄ ማድረጉ ይመረጣል።

ሸንጎው በዚህ ጉዳይ ላይ አቋም መውሰዱ ትንሽ የተጣደፈ ይመስለኛል።በሁለቱም ፓርቲዎች በኩል ያልተጠናቀቁ ብርቱ ጉዳዮች አሉ።ጅምራችሁ ጥሩ ነው!የሚለው የማበረታቻ ድጋፍ እንዳለ ሆኖ ነጻና ዴሞክራሲያዊ ውይይት ያስተናገደ፣የአባላቱን ተሳትፎ ያረጋገጠ ፣በኢትዮጵያ ብሄራዊ አጀንዳ ዙሪያ ያሉትን ሕዝባዊ ጥያቄዎች በየፈርጃቸው የተነተነና መልስ የሚሰጥ ሰነድ ይፋ ሆኖ መቅረብ አለመቅረቡን መጠየቅ የተገባ ነው።ይህ ሳይሆን ፓርቲዎቹ ወደፊርማ ደጋፊዎችም ወደሙገሳው መሮጥ አይኖርባቸውም።በተያዘው እሩጫ ከተቀጠለ የኢትዮጵያዊነት ጭላንጭል የሚታይበት መኢአድ ለመከራ መጋለጡ አይቀሬ ነው።በኢትዮጵያዊነት ዙሪያም ጥቁር ደመና እንዲያንዣብብና እንዲዳከም ዕድል ይፈጥራል።

ሸንጎው ለትብብርና ለአንድነት ካለው ጽኑ ፍላጎት ጎን ለጎን ትብብሩ የሚሳካበትንና የሚጠነክርበትን መንገድ ማሳየትና ምክር መለገስ ይኖርበታል።ለሚሰነዝረውም ምክር ከላይ የተጠቀሱት የውድቀት ምልክቶች ሊሆኑ ይችላሉ ብዬ ያስቀመጥኳቸውን ነጥቦች ሊገለገልባቸው ይችላል።ሸንጎው ጥራትና ዓላማ ላለው፣ሸፍጥና ክህደት ለማይኖርበት እውነተኛ ውህደት በምክርና በእርማት ሊረዳ ይችላል።

ይታያል በላቸው

አውሮፓ

25-06-2014